የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሁለተኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ ታህሳስ ፰ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

22nd Year No.19
ADDIS ABABA 18th December, 2015

ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፰ ዓ.ም

"የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ …ገጽ ፰ሺ፯፻፲፮

Regulation No. 367/2015".

Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation" Establishment Council of Ministers Regulation ………..……Page 8716

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፰

## የኢትዮጵያ ማዕድን፣ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፰ አንቀጽ ፭ እና የመንግስት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፫፻፷፯/፪ሺ፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

፩/ "ነዳጅ "ማለት ከኦይል ሼል ወይም ከታር ሳንድ የተገኘውን ሀይድሮ ካርቦን ጨምሮ የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት እና የተፈጥሮ ጋዝ ሲሆን ከሼል ጋዝ፣ ከድንጋይ ከሰል እና ከባዮፌዩል ሥራዎች የሚመረቱ ተመሳሳይ ምርቶችን ያካትታል፤

፪/ "የነዳጅ ሥራዎች" ማለት ድፍድፍ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ መፈለግ፣ማልማት፣ ማውጣት፣ ማምረት፣ በመስክ መለያየት፣ ማዘጋጀት፣ ማከማቸት፣ ወደ ውጭ ሀገር እስከሚላክበት ወይም ለአገር ውስጥ ፍጆታ ወደሚሰራጭበት ሥፍራ ማጓጓዝ እና ለገበያ ማቅረብ ሲሆን

Council of Ministers Regulations No.367/ 2015

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO ESTABLISH THE ETHIOPIAN MINERAL, PETROLEUM AND BIO-FUEL CORPORATION

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 916 / 2015 and Article 47(1) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/ 1992.

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the "Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation" Establishment Council of Ministers Regulations No. 367/2015".

### 2. Definition

1/ "petroleum" means crude oil and natural gas and includes hydrocarbons produced from oil shale and tar sands; it shall also encompass similar products produced from shale gas,coal and bio-fuel operations;

2/ "petroleum operations" means the operations involving and related to the crude oil and natural gas exploration, development, extraction, production, field separation, treatment, storage, transportation up to the point of exportation or entry into a system for domestic consumption, and marketing of petroleum, including processing of natural gas and refining of crude oil;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

ከተፈጥሮ ጋዝ የተለያዩ ምርቶችን ማውጣትና የነዳጅ ድፍድፍ ዘይት ማጣራትን ይጨምራል፤

፫/ “ማዕድን” ማለት ማናቸውም ዋጋ ያለው በጠጣር፣ በፈሳሽ ወይም በጋዝ መልክ በተፈጥሮ በመሬት ላይ ወይም ውስጥ፣ በውሃ ውስጥ ወይም ስር የሚገኝ የጂኦሎጂ ሂደት ወይም ሁኔታዎች የተፈጠረ ሲሆን ቀደም ሲል ተቆፍሮ በወጣና ተርፎ የተቆለለ ማዕድን አዘል አፈር ወይም በቀሪ የማዕድን ክምችቶች ውስጥ የሚገኝ ማዕድንን ይጨምራል፤ ሆኖም የሚከተሉትን አይጨምርም፦

ሀ) ለመታጠቢያ፣ ለመዝናኛ፣ ለሕክምና ከሚውል የጂኦተርማል ውሃና ከውስጡ ማዕድን ለማውጣት ከሚውል እንደብራይን ውሃ በስተቀር ሌላውን ውሃ፤

ለ) አግባብ ባለው የነዳጅ ሕግ ትርጓሜ የሚካተቱ የተፈጥሮ ዘይትና ጋዝ፤

ሐ) ለም አፈርን እና ነዳጅ አዘል አካላትን፡፡

፬/ “የማዕድን ሥራዎች” ማለት የማዕድናት ቅኝት፣ ምርመራ፣ ይዞ መቆየት፣ ወይም ማምረት ጋር የተያያዙ ተግባራት ሲሆን በከበሩ ማዕድናት ግብይት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶፩/፪ሺ፩ መሠረት የማዕድናት ግብይት ሥራዎች መሥራትን ያካትታል፤

፭/ “የባዮፌዩል ሥራዎች” ማለት ከሞላሰስ፣ ከተክሎች፣ ከእንስሳት ስብና ከሌሎች የተለያዩ ግብዓቶች ነዳጅ የማምረት ተግባር ነው፡፡

## ፫. <u>መቋቋም</u>

፩/ የኢትዮጵያ የማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ “ኮርፖሬሽን” እየተባለ የሚጠራ) የፌደራል መንግስት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮርፖሬሽኑ በመንግስት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል፡፡

## ፬. <u>ተቆጣጣሪ ባለስልጣን</u>

የመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ይሆናል፡፡

## ፭. <u>ዋና መስሪያ ቤት</u>

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ

3/ “mineral “means any mineral substance of economic value, whether in solid, liquid or gaseous form, occurring naturally on or within the earth or in or under water and which was formed by or subjected to an ecological process, and includes any mineral occurring in residue stockpiles or in residue deposits, but excludes:

a) water, other than geothermal water that may be used for bathing, recreational and therapeutic purpose or water used for the extraction of any mineral such as brine;

b) natural gas and petroleum as defined in the relevant petroleum law;

c) top soil and oil shale;

4/ “mining operations” means any activity associated with or connected to reconnaissance, exploration, retention, or mining and includes engaging in transaction in accordance with the Transaction of Precious Minerals Proclamation No. 651/ 2009;

5/ “bio-fuel operations” means activities related to the production of fuels from various feed stocks including molasses, plants and animal fats.

## 3. <u>Establishment</u>

1/ The Ethiopian Mineral, Petroleum and Bio-fuel Corporation (here in after referred as the “Corporation”) is hereby established as a Federal Government Public Enterprise.

2/ The Corporation shall be governed by Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

## 4. <u>Supervising Authority</u>

The Ministry of Public Enterprise shall be the supervising Authority of the Corporation.

## 5. <u>Head Office</u>

The Corporation shall have its Head Office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere in the country as may be necessary.

## 6. <u>Objective of the Corporation</u>

The objectives for which the Corporation is established are:

እንደአስፈላጊነቱ በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል፡፡

**፮. <u>ዓላማ</u>**

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት ዓላማ የሚከተሉት ናቸው፦

፩/ በነዳጅ፣ በማዕድንና በባዮፌውል ሥራዎች ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ የአገሪቱን የተፈጥሮ ሀብት በተገቢ ሁኔታ በማልማት የበለጠ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፤

፪/ በዘርፉ አገር በቀል አቅምን በመገንባት በዘርፉ ለሚሰማሩ ሌሎች እገዛ ማድረግና ከዘርፉ የአገሪቱን ተጠቃሚነትን ማረጋገጥ፤

፫/ ከስትራቴጂካዊ አስፈላጊነታቸው አንፃር ከፍተኛ ግምት በሚሰጣቸውና በግሉ ዘርፍ ሊሟሉ በማይችሉ ዘርፎች ላይ በመሳተፍ ክፍተቱን መሙላት፤

፬/ ተወዳዳሪ የመንግስት ልማት ድርጅት በመሆን በአገሪቱ ኢኮኖሚ ግንባታ እገዛ ማድረግ፤

፭/ ራሱ ወይም እንደሁኔታው ከሌሎች ጋር በመሆን በማዕድን፣ ነዳጅና ባዮፌዩል ሥራዎች ኢንቨስትሜንት ላይ መሳተፍ፣ ማልማትና ማምረት፤

፮/ በሌሎች ባለሀብቶች በሚካሄዱ የነዳጅ፣ የማዕድንና የባዮፌዩል ሥራዎች ውስጥ ኢንቨስት ማድረግ፤

፯/ የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት አክስዮን መሸጥ ወይም መግዛት፤

፰/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያና የመንግሥት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ቦንድ መሸጥና ዋስትና የማስያዝ፣ ከአገር ውስጥና ከውጭ የገንዘብ ምንጮች ጋር የብድር ውል መደራደርና መፈራረም፤

፱/ ከማዕድን፣ ከነዳጅና ከባዮፌዩል ጋር የተያያዙ የማማከር፣ የድሪሊንግ፣ የላብራቶሪ፣ መረጃ የመሰብሰብ፣ የመተንተንና የመተርጎም፣ የአዋጭነት ጥናት ሥራዎችን መሥራት፣ ስልጠናና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን መስጠት፤

፲/ በአገር ውስጥና በውጭ አገራት ተወዳዳሪና አትራፊ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ እገዛ የሚያደርጉለትን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂና የዘመናዊ አሰተዳደር ግብዓቶችን ለማግኘት

1/ to ensure that the country benefits from its natural resources by developing and directly engaging itself in the mining, petroleum and bio-fuel sectors;

2/ to ensure the benefit of the country by building the local capacity of the sector and assisting others engaged in the sector;

3/ to fill the gap in the areas of investment which have strategic importance but are not addressed by the private sector;

4/ to contribute to the national economy upon being competent public enterprise;

5/ to engage in the investment, development and production of the mineral, petroleum and bio-fuel operations on its own or in association with others as appropriate;

6/ to invest in petroleum, mining and bio-fuel operations carried out by other investors;

7/ to sell or buy shares in accordance with the policy directions given by the Ministry of Public Enterprise;

8/ to sell and pledge bonds, to negotiate and sign loan agreements with local and interactional financial sources in accordance with the directives issued by the Ministry of Finance and Economic Cooperation and in line with the policy direction given by Ministry of Public Enterprises;

9/ to engage in the provision of services like consultancy, drilling, laboratory, data acquisition, processing and interpretation, feasibility study and training in the field of mining, petroleum and bio-fuel operations;

10/ to conduct study and implement when approved mechanisms that can equip the Corporation with the financing, technology and modern administrative inputs (including attracting or engaging in investments) which can help it to be competitive and profitable within the country or abroad;

11/ to engage in any other related activities necessary to attain its objectives in accordance with the direction of the Ministry of Public Enterprise.

የሚያስችለውን (ኢንቨስትመንት መሳብንም ሆነ በኢንቨስትመንት ላይ መሳተፍን ጨምሮ) ጥናት በማካሄድ የውሳኔ ሀሳብ ማቅረብ፣ ሲፈቀድ ተግባራዊ ማድረግ፣

፲፩/ በመንግስት ልማት ድርጅቶች ሚኒስቴር በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ሥራዎችን መሥራት፡፡

**፯. ካፒታል**

የኮርፖሬሽኑ የተፈቀደ ካፒታል ብር 15,267,000,000 (አሥራ አምስት ቢሊዮን ሁለት መቶ ስድሳ ሰባት ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር 4,017,000,000 (አራት ቢሊዮን አሥራ ሰባት ሚሊየን ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል፡፡

**፰. ኃላፊነት**

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም፡፡

**፱. ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ**

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል፡፡

**፲. የተሻረ ደንብ**

የኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፬/፪ሺ፬ በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡

**፲፩. የመብቶችና ግዴታዎች መተላለፍ**

የሚከተሉት የመንግስት ልማት ድርጅቶች መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፦

፩/ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፷፬/፪ሺ፬ የኢትዮጵያ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ድርጅት፣

፪/ የኢትዮጵያ የማዕድን ልማት አክስዮን ማህበር፡፡

**፲፪. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከታህሳስ ፰ ቀን ፪ሺ፰ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፰ ቀን/ ፪ሺ፰ ዓ.ም**

**7. Capital**

The authorized capital of the Corporation is Birr 15,267,000,000 (Fifteen Billion Two Hundred Sixty Seven Million Birr) out of which Birr 4,017,000,000 (Four Billion Seventeen Million Birr) is paid up in cash and in kind.

**8. Liability**

The Corporation shall not be liable beyond its assets.

**9. Duration of the Corporation**

The Corporation is established for unlimited period.

**10. Repealed Regulations**

The Ethiopian Petroleum and Natural Gas Development Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 264/2012 is hereby repealed.

**11. Transfer of Rights and Liabilities**

The rights and liabilities of the following public enterprises are hereby transferred to the Corporation:

1/ the Ethiopian Petroleum and Natural Gas Development Enterprise established under the Council of Ministers Regulations No. 264/2012;

2/ the Ethiopian Mineral Development Share Company.

**12. Effective date**

This Regulation shall enter into force on this 18th day of December, 2015.

**Done at Addis Ababa this 18th day of December, 2015.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

**ኃይለማሪያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**